QuickNotes mcps

የዊንተር አየር ጠባይ፡- ከMCPS አለመራቅ

የዊንተር አየር እየተቃረበ ነው። ወላጆች በአደገኛ አየር ሁኔታ ምክንያት ት/ቤት ስለሚዘጉባቸው፣ ዘግይተው ስለሚከፈቱበት እና ተማሪዎች አስቀድመው ስለሚለቀቁባቸው የሚማሩባቸው፣ MCPS የተለያዩ መንገዶች ያቀርባል።

- **AlertMCPS (MCPS-ተጠንቀቅ)**
  ከአየር ጋር የተገናኘ አስቸኳይ ሁኔታ ወይም ሌሎች በት/ቤት እንቅስቃሴ ተፅእኖ የሚኖራቸው ከባድ ክውነቶችን በሚከሰቱበት ወቅት Montgomery County Public Schools የሚልካቸው ቴክስት መልእክቶችም ሆነ ኢሜይሎችን ተቀበሉ። ወላጆች በተለይ የልጆቻቸውን ት/ቤቶች የሚመለከቱ ማስጠንቀቂያዎች ለመቀበል በኮምፒውተር መመዝገብ ይችላሉ።
  ለAlertMCPS ተመዝገቡ

- **የMCPS መነሻ ገፅ**
  www.montgomeryschoolsmd.org

- **የQuickNotes የኢሜይል ዜና አገልግሎት**
  ተመዝገቡ በwww.mcpsquicknotes.org

- **የMCPS ኬብል (ቲቪ) ቻነሎች**
  Comcast 34፣ Verizon 36 ወይም RCN 89

- **የተዘገበ መረጃ**
  301-279-3673

- **MCPSን ጠይቁ**
  301-309-6277። ሰራተኞች ከሰኞ እስከ አርብ ከ7:30 a.m. እስከ 5:30 p.m በእንግሊዝኛና ስፓኒሽ ጥሪ ይቀበላሉ።

- **Twitter**
  http://twitter.com/mcps

- **ያካባቢ ሬድዮና ቲቪ ጣብያዎች**

የአስቸኳይ ግዜ መገናኛ መረጃዎች በልጅዎ ት/ቤት ማህደር ወቅታዊ መሆኑን እባክዎ ያረጋግጡ።

የMCPS አስቸኳይ ሁኔታ መረጃ አቀባበል

የበላይ ተቆጣጣሪ  የ$1.55 ቢልዮን የህንፃ ፕላን ሀሳብ ያቀርባል

የበላይ ተቆጣጣሪ ጄሹዋ ፒ ስታር የ$1.55 ቢልዮን Capital Improvements Program (ካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም) (CIP) ያቀርባል ይህም፣ በሚመጡት ስድስት አመቶች፣ ለMCPS  በመቶዎች የሚቆጠሩ መማርያ ክፍሎችን ይጨምራል የምዝገባ በተአምራዊ ደረጃ መናር ያስከተለውን መጨናነቅም ያቃልለዋል።

የዶ/ር ስታር ያቀረበው CIP ትኩረት የሚሰጠው የመማርያ ክፍሎችን በመጨመርና በማርጀት ላይ የሚገኙ መሰረተ ልማቶችን፣ ማሞቅያ፣ አየር ማስተላልፍያ፣ እና አውቶማቲክ ማሞቅያና ማቀዝቀዣ (HVAC) ስርአቶችን ጨምሮ፣ ማደስ ላይ ነው። የዶ/ር ስታር CIP ቀድሞ የፀደቁ የህንፃ ፕሮጀክቶንም በፕሮግራም ይዟል።

የMCPS ምዝገባ ባለፉት ስድስት አመቶች በ14,000 አካባቢ ተማሪዎች አድጓል፣ አብዛኛው የዚያ እድገት፣ 90 በመቶ የሚደርስ፣ የተፈፀመው በኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች ነው። በሚመጡት ስድስት አመቶች፣ የMCPS ምዝገባ እድገት በ11,000 ተማሪዎች እንደሚሆን ይጠበቃል። በዚያን ወቅት፣ የMCPS ምዝገባ በሜሪላንድ ውስጥ ከማንኛውም ዲስትሪክት በላይ ጨምሯል።

"ይህ CIP የዲስትሪክታችንን ተአምራዊ የቦታ ጥያቄ ይጋፈጠዋል እናም፣ በጠርዛቸው ለመፈንዳት ተቃርበው የሚጋኙትን የኤሌሜንታሪ ት/ቤቶቻችን የተወስነ ማስታገሻ ያቀርቡለታል፣" ብለው ዶ/ር ስታር ተናገሩ። "ቢሆንም፣ ዛሬ እዚህ ለሚገኙትና ለወደፊት ለሚመጡት ተማሪዎች የ21ኛው ክፍለ ዘመን የመማርያ መገልገያዎች የምናቀርብ ከሆነ ለወደፊት ተጨማሪ የመዋእለ ንዋይ ፈሰስ እንድናደርግ ይፈለግብናል።"

ዶ/ር ስታር ያቀረበው የ%1.55 ቢልዮን CIP አሁን ካያዝነው CIP (ከ2013-2018 የበጀት ዘመን) የ$183.9 ሚሊዮን ጭማሪ ያሳያል፣ ነገር ግን ከዲስትሪክቱ ተጨባጭ ፍላጎት በጣም ያነሰ ነው። የዲስትሪክቱን አንገብጋቢ መገልገያ፣ ታህታይ መዋቅር፣ እና የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች ለማሟላት የ$2.2 ቢልዮን CIP ያስፈልጋል።

ሀሙስ ኦክቶበር 31፣ ዶ/ር ስታር እና የትምህርት ቦርድ ፕሬዚደንት ክሪስቶፈር ባርክሌይ የMontgomery County ስራ አስፈፃሚ አይዛያ ሌጌትን፣ የካውንቲ ምክር ቤት ፕሬዚደንት ናንሲ ናቫሮ እና በርካታ የስቴት፣ ያካባቢ እና የካውንቲ ባለስልጣኖች የሜሪላንድ አጠቃላይ ምክር ቤትንና ጎቨርኖር ማርቲን ኦ'ማይሊን ገፋፍቶ ለMCPS የትምህርት ቤት ህንፃ ገንዘብ ለማስጨመር ተገናኝተዋል።

በየሁለት አመት አዲስ የስድስት አመት CIP ይፀድቃል እናም በአራት አጠቃላይ ክፍሎች የመዋእለነዋይ ፈሰስ ያካትታል — እንደ አዲስ ት/ቤቶችን ተጨማሪ መማርያ ክፍሎች የመሳሰሉ የስፋት አቅም ፕሮጀክቶች፤ ነፍስ-ዘሪ/የመስፋፋት ፕሮጀክቶች ያሉትን ትም/ቤቶች የሚያድሱና የሚያስፋፉ፤ ታህታይ መዋቅር ማሻሻያዎች፤ እና ቴክኖሎጂ።

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ የዶ/ር ስታርን ረቂቅ ይገመግማል የCIPውን ጥይቁ ሰኞ ኖቨምበር 18 ያፀድቃል። ከዚያም ያ ጥያቄ ለካውንቲው ስራ አስፈፃሚና የካውንቲ አማካሪ  ለግንዛቤ ገቢ ይሆናል። ቦርዱ፣ የCIP ጥያቄን በሚመልከት ተገኝታችሁ ሀሳባችሁን ለማጋራት እድል የሚኖራችሁ የመጨረሻውን ህዝባዊ ችሎት ሀሙስ ኖቨምበር 14 ያከናውናል። ተጨማሪ መረጃ በቦርዱ ህዝባዊ ተሳትፎ ድር ጣብያ ይገኛል።

**መስቀል ወይም እጅ- ነፃ**

ከኦክቶበር 1 2013 ጀምሮ፣ በሜሪላንድ ከዳር እስከዳር ያለእጅ-ነፃ በእጅ በተያዘ ሴል ፎን እየተጠቀሙ መኪና ስለነዱ ብቻ የትራፊክ መኮንኖች ቲኬት ይሰጣሉ። ለመጀምርያ ጥፋት መቀጮ $83 ሲሆን ለተከታይ ጥሰቶች ይጨምራል። Montgomery County Public Schools (MCPS) ይህን አዲስ ህግ በሚመለከት መልእክቱን ይፋ ለማድረግ ከMontgomery County ፖሊስ መምርያ ጋር አብሮ እየሰራ ነው። ይህን ቃል በመዘርጋት እና ከወጣት ነጂዎ ጋር መረጃውን መጋራት አስፈላጊ ነው። አብረን፣ እጆቻችንን መሪው ላይ አንጂ፣ ቴሌፎኑ ላይ ባለማድረግ፣ መንገዶቻንን ይበልጥ ጤናማ እንዲሆኑ ማገዝ እንችላለን።

[ተጨማሪ ይማሩ]()

**ከበላይ ተቆጣጣሪው ጋር የሚመጡ ክውንውኖች**

የበላይ ተቆጣጣሪ ጆሹዋ ስታር በሚመጡት ወራት በርካታ የሰበካ ጉብኝት ያደርጋል። እነዚህ ክውነቶች — የማህበረሰብ ቀኖች፣ የተማሪ ታውን ሆል (የከተማ አዳራሽ) እና የደወል ሰአቶች መድረኮች የሚያካትቱ — ለMCPS ህብረተሰብ ጥያቄዎችን የማቅረብና ሀሳባቸውን የማጋራት እድሎችን ይሰጣሉ።

***የማህበረሰብ ቀኖች***

ዶ/ር ስታር የሚቀጥለውን የማህበረሰብ ቀን ክውነት ሃሙስ ኖቨምበር 21 በዳውንታውን ኮንሶርሽየም (Montgomery Blair፣ Albert Einstein፣ John F. Kennedy፣ Northwood እና Wheaton ክምችቶች)። የታውን ሆል ስብሰባ በMontgomery Blair High School, 51 UniversityBlvdEast in Silver Spring በ7:30 p.m. ይከናወናል። ለሚቀጥሉት ሁለት የማህበረሰብ ቀኖች እለቶችና የከተማ አዳርሽ እለትና ቦታ የሚከተሉት ናቸው።

- ሰኞ ፌብሩዋሪ 3 2014፡- Bethesda-Chevy Chase, Winston Churchill, Richard Montgomery, Rockville, Walter Johnson, Walt Whitman እና Thomas S. Wootton ክምችቶች; ታውን ሆል፡ Winston Churchill High School

- ሰኞ ኤፕሪል 28 2014፡- Northeast Consortium (James Hubert Blake, Paint Branch እናSpringbrook), Col Zadok Magruder እና Sherwood clusters; ታውን ሆል በPaint Branch High School

***የተማሪ ታውን ሆሎች***

የሚቀጥለው ታውን ሆል፣ ሰኞ ኖቨምበር 25 በA. Mario Loiederman Middle School እንዲሆን ተወስኗል። የተማሪ ታውን ሆል ስብሰባዎች ዶ/ር ስታርን ለነሱ አስፈላጊ ስለሆኑ ጉዳዮች በቀጥታ ከተማሪዎች ለመስማት እድል ናቸው። እነዚህን ክውነቶች የሚያስተናግደው፣ በትምህርት ቦርድ የተማሪዎች ተጠሪ፣ Justin Kim (ጀስቲን ኪም) ነው። በMCPS ድር ጣብያ ይመዘግባሉ በMCPS ቲቪም ይታያሉ።

የተቀሩት የተማሪ ታውን ሆሎች እለትና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ማክሰኞ ጃኑዋሪ 28 Northwood High School
- ሀሙስ ፌብሩዋሪ 27 Rosa Parks Middle School
- ማክሰኞ ማርች 18 Watkins Mill High School
- ሀሙስ ኤፕሪል 24 Herbert Hoover Middle School

ተጨማሪ መረጃ በዚህ ይገኛል www.mcpsstudenttownhall.org።

***የደወል ሰአቶች***

በሚቀጥሉት በርካታ ወራት ስለት/ቤት መጀመርያና መጨረሻ ሰአቶች ስለቀረበው ለውጥ አስተያየቶች ለማቅረብ MCPS በርካታ እድሎች ይሰጣል። ይህም የማህበረሰብ መድረኮች፣ የትኩረት ቡድኖችና መጠይቆችን ያካትታል። የመጀመርያው የማህበረሰብ መድረክ ኦክቶበር 28 ተከናውኗል። የሌሎቹ ሶስት ማህበራዊ መድረኮች እለቶችና ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- **ሰኞ ዲሰምበር 16፡-** Richard Montgomery High School, 250 Richard Montgomery Drive in Rockville
- **ሰኞ ጃኑዋሪ 6፡-** Seneca Valley High School, 19401 Crystal Rock Drive in Germantown
- **ሰኞ ፌብሩዋሪ 10፡-** Montgomery Blair High School, 51 University Blvd, East, in Silver Spring

ሁሉም መድረኮች የሚከናወኑት ከ7–8:30 p.m ነው። የህፃናት እንክብካቤ (4 አመት እና ከዚያ በላይ) እና የትርጉም አገልግሎቶች ይቀርባሉ። ለተጨማሪ መረጃ የደወል ሰአቶች ድር ጣብያ ጎብኙ።

በቅርብ ግዜ የሚመጣ፡- ለማመልከቻ ፈተና - ፕሮግራሞች ብቻ

Montgomery Blair፣ Richard Montgomery፣ እና Poolesville 2ኛ ደረጃ ት/ቤትች፣ እንዲሁም Roberto Clemente፣ Eastern፣ እና Takoma Park መለስተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለማመልከቻ-ብቻ ፕሮግራሞች የተፈፀመ ማመልከቻ ላቀረቡ ተማሪዎች ፈተና ለዲሰምበር 7 ተቀጥሯል። ስለ ሰአቶችና ቦታዎች የማመልከቻውን ፎርም ተመልከቱ።

ለኤሌሜንታሪ Highly Gifted Centers (ከፍተኛ ተሰጥኦ ማእከሎች) ፈተና በጃኑዋሪ ወር በአካባቢ ት/ቤቶች ይሆናል።

ተጨማሪ መረጃ

የMCPS ተማሪዎች ያገለገለ መኪና ያዝ (Hold Used Car)፣ የኮምፒውተር ሽያጭ

የMontgomery County Students Automotive Trades Foundation (የተማሪዎች የአውቶሞቢሎች ንግድ ተቋም) (ATF) እና የInformation Technology Foundation (የመረጃ/ኮምፒውተር ቴክኖሎጂ ተቋም) (ITF) ተማሪዎች ያደሷቸውን ያገለገሉ መኪኖችና ኮምፒውተሮች ዲሰምበር 24 ከ9-11 a.m. Damascus High School ይሸጣሉ።

ለሽያጭ ስለሚቀርቡ መኪናዎች ተጨማሪ መረጃ ኬሊ ጆንሶንን (Kelly Johnson) በ301-929-2197 ይጠይቁ፣ ወይም www.atfcareers.org ጎብኙ። ለሽያጭ ስለሚቀርቡ ኮምፒውተሮች ተጨማሪ መረጃ፣ www.itfcareers.org ጎብኙ

መኪኖቹና ኮምፒውተሮቹ የታደሱት የመማርያ ክፍልና የላቦራቶሪ አካል በመሆን በተማሪዎች ነው።

የማህበረሰብ አባላት ለፕሮግራሙ ተሽከርካሪዎች እንዲሰጡ ተጋብዘዋል። መኪኖችን የautomotive ፕሮግራም ባላቸው በDamascus፣ Gaithersburg፣ Seneca Valley ወይም Thomas Edison የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች መስጠት ይቻላል። ስጦታዎ ከአገርውስጥ ገቢ ቅነሳ ሊታሰብ ይችላል።

Automotive Trades Foundation
(የአውቶሞቢሎች ንግድ ስራ ተቋም)
Information Technology Foundation, Inc.
(የመረጃ ቴክኖሎጂ ተቋም የንግድ ማህበር)

ኖቨምበር 23 ከመላ አለም የፈረንሳይ-ተናጋሪዎች ባህሎች በአል አክብሩ

በMontgomery County የፈረንሳይ ቋንቋ እና ባህል አምስተኛዊውን አመታዊ የፍራንኮፎን በአል ኖቨምበር 23 አክብሩ። ክውነቱ የሚከናወነው ከ10 a.m. – 2:30 p.m በActivity Center፣ Bohrer Park, 506 S. Frederick Avenue in Gaithersburg ነው። የኪነት ዎርክሾፖች፣ ትክክለኛ መዝናኛዎች፣ መለስተኛ ግጥሚያዎች፣ የአእምሮ ችሎታ ውድድር እና ሌላም የሚያካትቱ ለጠቅላላ ቤተሰብ የሚሆኑ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ይኖራሉ።

በአሉ የተጀመረው በአነስተኛ የMCPS ፈረንሳይ አስተማሪዎች ቡድን ሁሉንም የፈረንሳይኛ መምህራንና ተማሪዎቻቸውን በማህበረሰቡ ውስጥ የፈረንሳይ ቋንቋና ባህል እንዲያበስሩ ነው። በአሉ የተጀመረው በ 2007 ነው።

ለተጨማሪ መረጃ፣ http://francophonefestival.org/ ጎብኙ።